# “ለሁሉም ጊዜ አለው”

ይህን ውብ አነጋገር ለዓለም ያበረከተው ከብዙ አመታት በፊት ጠቢቡ ሰሎሞን እንደሆነ ይታወቃል። ተወልጄ ባደግኩባት በይርጋለም፣ “ጊዜ ያመጣውን ጊዜ ይመልሰው አገረሰላምን ይርጋለም ወረሰው!” ሲሉ በልጅነት እሰማ የነበረውን አድጌ ከአባቴ ጠይቄ ስረዳ፣ ቀደም ሲል ጥንት የሲዳሞ ዋና ከተማ አገረሰላም ነበች። በጣሊያን ወረራ ጊዜ ታላቅ ተጋድሎ ያደረጉት ጀግናው ራስ ደስታ ዳምጠ በወቅቱ ይርጋለምን ስትራተጂክ ቦታ አድርገው ይዘው ስለነበር ቦተዋ ከርሳቸውም በኋላ ወደ ከተማነት እያደገች በመምጣት የክፍሉ ዋና ከተማ ሆና አገረሰላምን በመተካቷ ነው አባባሉ የተነገረው። ከዚያም ጊዜውን ጠብቆ ይርጋለም ደግሞ በአዋሳ ተተካች።

እንግዲህ ከነዚህ አባባሎች መረዳት የሚቻለው ምንም ባይመስለን፣ ምንም እልህ ቢያስጨርሰን፣ ብቻ ምንም ይሁን ምን ወቅቱን ጠብቆ ያ ጊዜ መድረሱ እንደማይቀር ነው። ጊዜው ሲደርስ ግን የዚያን ጊዜ ሲደሰቱና ሲያንጓጥጡ የነበሩት ሁሉ ያለቅሳሉ፣ ይሸማቀቃሉ። በአንጻሩ ደግሞ ያለቅሱ የነበሩት፣ አይናቸውን ወደ ሰማይ አንጋጠው ያንተ ያለህ ይሉ የነበሩት ሁሉ ይደሰታሉ፣ ቀና ብለውም ይሄዳሉ።

ለዚህ ጽሁፍ መነሻ ያበቃኝ፣ ሌላ ምንም ሳይሆን፣ ኢትዮጵያ ዛሬ በተባለው ዌብሳይት ላይ፣ “የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አስተዳደር በዳይሬክተሩ ታምሶአል” በሚል ርዕስ ስለዳይሪክተሩ ስለአቶ ዳኛቸው ካሳ የሙስና ጉድ ያወጣው ዜና ነው። ስለዚህ በበኩሌ የማውቀውን በበለጠ ግልጽ ለማድረግ ብዬ እንደሚከተለው ጠቃቅሻለሁ።

ይህ ሰው ወደ ፌዴራል ፍ/ቤቶች አስተዳደር ብቅ ያለው 1996 ዓ.ም ላይ ነው። ከርሱ በፊት የፍ/ቤቱ አስተዳደር ሃላፊ የነበሩት አቶ ተክሉ የሚባሉ ሰው ነበሩ። በ1994 ዓ.ም አገር አቀፍ የአስተዳደር ማሻሻያ ተብሎ አንድ ፕሮግራም ሲቋቋም በፌዴራል ፍ/ቤቶችም እንደዚሁ የፍ/ቤቶቹ ማሻሻያ ፕሮግራም ተቋቁሞአል። በወቅቱ እኔ ከፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ዳኞች አንዱ ነበርሁ። እናም ከጠቅላይ ፍ/ቤት የፍ/ቤቶቹ ማሻሻያ ጽ/ቤት ሃላፊ ሆኜ ተመረጥሁ። ልክ እኔ ተመርጬ ቢሮ እንደያዝሁ ከያለበት የአስተዳደር ሃላፊውን አቶ ተክሉን በሚመለከት የቅሬታ ደብዳቤዎች መያዝ እስከሚያቅተኝ ድረስ ይጎርፉ ጀመር። በወቅቱ ከእኔ ጋር እንዳጋጣሚ ሆኖ ቁራጥ ዳኞች ከከፍተኛ ፍ/ቤት ደበበ አሁን ጥሎ ወጥቶአል፣ እና ሰሎሞን የሚባል ከፌዴራል የመጀመሪያ ፍ/ቤት አሁን የከፍተኛ ፍ/ቤት ዳኛ(እፍ/ቤት ይኑር አይኑር አሁንአላውቅም) ነበሩ። በጉዳዩ ላይ ከራሱ ጭምር ማስረጃዎችን ሰማን። ተዛማጅ ማስረጃውችንም ሁሉ ሰበሰብን;፡ በተለይ የጠቅላይ ፍ/ቤት ሹፌሮች ግለሰቡ ከነዳጅ ጋር ያለውን ሙስና በፍ/ቤቱ ጊገር በኩል ደግሞ ከባለሻጮች ጋር ግለስቡ ሲያደርጋቸው የነበረውን ሙስናን በተመለከተ የቀረበው ጥቆማ በማስረጃዎች በማስደገፍ ሪፖርትና የውሳኔ አሳብ አጠናክሬ አሰፈላጊው ርምጃ በግለሰቡ ላይ ይወሰድ ዘንድ በወቅቱ የፍ/ቤቱ ጸረሙስና ተጠሪ ለነበረው አሁን የዳኛቸውን ጉዳይ ከሚያጣሩት አንዱ የሆነው መድኅን ኪሮስ ስጽፍ ግልባጭ ለጠቅላይ ፍ/ቤት ም/ፕሬዚዳንት ለአቶ መንበረፀሐይ ታደሰ አደረግሁ።

ከዚህ ቀደም ብሎ ገና ጉዳዩ እንደተጀመረ አቶ መንበረፀሐይ ምንድነው በዚህ ሰው ላይ ዘመቻ የምታካሂድበት በሚል ምርመራውን እንዳቆም ዓይነት ግሳጼ ለማድረግ ሞክሮ ነበር። ሆኖም የውሳኔው ግልባጭ እንደደረሰው ጠርቶኝ አንተም በትግሬዎች ላይ ዘመቻ ጀመርክ እንደ በማለት ሲወርፈኝ እንዴት? ብዬ ጠየቅሁት። በሠራተኞቹ ስብሰባ ላይ ስሰደብ ምንም የወሰዳችሁት ርምጃ የለም። በተክሉም ላይ የመስከሩት ድርጊቱን ፈጽሞ ሳይሆን፣ የትግሬ ጥላቻ ነውና ይህንኑ እንዴት ትቀበለዋለህ? በሚል የቁጣ አነጋገር

ተቀበለኝ። እኔም በወቅቱ ስለማጣራቱ ትክክለኛነት በማረጋገጥ በኔ በኩል ጨርቸሼአለሁ በማለት ከቢሮው በብስጭት ወጣሁ። ከዚያም ሳልቆይ በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በም/ፕሬዚዳንትነት ተሹሜ ከቦታው ለቀቅሁ። በኋላም ይህንኑ የፌዴራል ፍ/ቤቶችን የፍ/ቤት ማሻሻያ ፕሮግራምን ደርቤ እስከለቀቅሁ ድረስ እንድሰራ ተደረግሁ። በጉዳዩ ላይ ዝምታ ሰፍኖ ስለነበር የፍ/ቤቱን የጸረሙስና ሃላፊውን አቶ መድኅንን፣ በሌላ በኩል ደግሞ አቶ ከማልን ሁኔታው ያለበትን እየነገርኳቸው እጨቀጭቅ ተያያዝሁ። የጸረሙስናው ተወካይ ለጸረሙስና ኮሚሽን እንዲያመለክትና ርምጃ እንዲያስወስድ፣ አስተዳደሩ ደግሞ የራሱን ርምጃ እንዲወስድ ነበር አነሳሴ።

ሆኖም በመሃሉ አንድ ቀን ከሥራ ወጥቼ ወደ ቤቴ በመጓዝ ላይ እንዳለሁ ስልክ ተደዉሎ የጠቅላይ ፍ/ቤቶች ሾፌሮች በሙሉ ታስረዋልና ቶሎ ድረስ ተባልኩ። ወደ ላምበረት ደርሼ የነበርሁ ቢሆንም፣ ደንግጬ ምን ሊሆን ይችላል ብዬ መኪና አዙሬ እጠቅላይ ፍ/ቤት ሄድሁኝ። ሰሎሞን እዚያው ስለነበር አብረን ተያይዘን ነገሩን ለማወቅ ወደ አቶ መንበረፀሐይ ቢሮ ገባን። ይህን ጊዜ እኔ እንዳሳሰርኳቸው ቆጥረህ አይደል ወልዴ በዚህ ሰዓት የመጣኸው አለኝና ይህንኑ ተመልከት ብሎኝ የነዳጅ ኩፖችን መውሰጃ ኮፒ ሰነዶችን ሰጠኝ። አሁን ትዝ እንደሚለኝ ወደ አምስት ሾፌሮች ፎርጅድ በሆነ አካኋን በኩፖን ያጭበረበሩበት ነው በማለት በስማቸው ግርጌ ፊርማቸው ነው የሚል ምልክት አየሁኝ። ከአቶ ተክሉ ጋር ራሳቸው የሰሩት ፎርጅድ መሆኑን በወቅቱ ከሰሎሞን ጋር ብንጠርጥርም በሕግ በመያዙ ምንም ነገር ለማድረግ አልተቻለም። እና እንዴት ያሉ ልጆችን በአቋራጭ ቁርስ መንበረና ተክሉ አደረጓቸው። ይህ ከአቅሜ በላይ ቢሆንም በተክሉ ላይ የተደረሰውን ምርመራ ውጤትን በተመለከተ ሳልታክት በመቀጠሌ ነገሮችን ለመሸፋፈን ያህል በግዳጅ ያለዕድሜው ሰውዬው ጡረታ እንዲወጣ አድረገው አስወጥቱና በዚሁ የጸረሙስና ሃላፊው የአቶ መድኅን ቸልተኝነት ታክሎበት ተድበስብሶ ቀረ።

ከዚህ በኋላ የከፍተኛ ፍ/ቤት አስተዳደር ሃላፊ <u>ወ/ሮ የሺ</u> የተባለች ባላት ልምድና ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ ወደ ፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በተክሉ ቦታ አድጋ አስተዳደሩን ያዘች። በእዉነቱ እስከማውቀው ድረስ የፍ/ቤቶችን አስተዳደር በዘመናዊ አሰራር ለመተካትና የበላይ ሃላፊዎችንም ጥልቃ ገብነት ለማስወገድ ደፋ ቀና በምትልበት ወቅት የፈጸመችው ምንም ዓይነት ጥፋት ሳይኖርና ሳይታይ በአቶ ዳኛቸው ካሳ ተተካች። ገና ከመግባቱ አቶ ዳኛቸው ፍ/ቤቱን አተረማመሰው። <u>መሪ ምን ጊዜም ትክክል ነው(The boss is always right)</u> በሚለው መፈክሩ የነ አቶ መንበረጸሐይን ልቦና እየገዛ በመምጣት፣ እኛ የየፍ/ቤቶቹ የበላይ ሃላፊዎች እያለን ሠራተኞቻችንን ከወዲያ ወዲህ ያንጓልሏቸው ጀመር። ለነገሩ የማስተዳደር ሃላፊነቱ የየፍ/ቤቶቹ ቢሆንም፣ ለሁሉም ፍ/ቤቶች ሠራተኖችን በማዕከል የሚቀጥረውና የሚያሰናብተው የጠቅላይ ፍ/ቤት አስተዳደር ነው።

ይህኑን መግቢያ መሠረት አድርጎ ነው የተነሳው። ምንም እንኳ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት አቶ ከማል በድሪ ቢሆኑም፣ በዋናኛነት ፍ/ቤቱን የሚያስተዳድረውና የሚያሽከረክረው ምክትሉ አቶ መንበረጸሓይ ታደሰ ነው። ፍ/ቤቱ የማንም መጫወቻ እንዲሆን ያደረገው ይኸው ሰው ነው። ኸረ አንድ ነገር አቶ መንበረ አድርግ ይህ ሰው ከአሁኑ ሠራተኞችን እረፍት ነስቷቸዋል፣ ነገሮች ከቁጥጥር ውጭ ከመውጣታቸው በፊት፣ ይህ ሰው ሊገታ ይገባል እያልኩኝ ባሳስብም ልሰማ አልቻልኩም። ለቅርብ አለቃዬ ለአቶ ደሳለኝ በርሄ ሁኔታዎችን እያነሳሁ ብወተውትም እባክህን ይህ ሰው በጣም አዋቂ ነው፣ መሪው ሁልጊዜ ትክክል ነው የሚለውን መፈክሩን መከተል አለብን፣ ዝም ብለን መንገዱን ልቅ አድርገን ተጎድተናል አንድ ቀን ሲለኝ ተስፋ ቆረጥሁ። በተለያዩ መንገዶች ከሥሬ የነበሩትን ሠራተኞችን የማድንበትን ብቻ መቀያየስን

ተያያዝሁ። አማራጭም አልነበረኝምና።እንግዲህ የአቶ ዳኛቸው አገባብና አነሳስ በጥቂቱ እንዲህ ነበር ለማለት ነው።

አቶ ዳኛቸው ግን በዚህ በዚህ የልብ ልብ የተሰማው ጭቃ ጅራፉን በመለዋወጥ ቀጠለበት። ያችን የአስተዳደር ሃላፊ የነበረችውን የሺንና የጠቅላይ ፍ/ቤት የፋይናንስ ሃላፊ የነበረውን አቶ መስፍን የተባለ በፍ/ቤቱ ብዙ የቆየና ልምድ ያለውን በአየር ላይ አስቀመጣቸው። ምነው ያለውም ሃልፊ ጠፋ። የትም በእውቀቱ መሆን የሚችለውን ወልደጊዮርጊስ የተባለ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሚሰራውን እንደአዙሪት ከላይ ወደታች ያንኳልለዋል። ይህ ሠራተኛ ልዩና ፈጣን ሁለገብ የሆነ በንጹህ ሕሊና የሚሰራ ወጣት ነው። እኔ ወደ መውጫዬ አካባቢ ቀደም ብሎ ሾፌሬ የነበረውና በሥነ-ምግባሩና ባለው የሜካኒክ ዕውቀቱ የጠቅላይ ፍ/ቤት የትራንስፖርት ሃላፊ ሆኖ የነበረውን ሠራተኛ ወደ ከፍተኛ ፍ/ቤት አውርዶት እንደነበረ ሰማሁ። ሌሎችም በብዛት በእንዲህ የተሰናከሉና እየተሰናከሉ ያሉ እንደማይጠፉ እገምታለሁ። ይህ አድራጎት አጠቃላይ የፍ/ቤቱን ሥራ ሽባ የሚያደርግ አካሄድ መሆኑን ማንም ሊገነዘበው ይችላል።

እኔ የፌዴራል ፍ/ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም መመሪያም ምክትል ሃላፊ ነበርሁ። አንድ ቀን ትመስለኛለች ሰላማዊት የምትባል ከጠቅላይ ሸርዓ ፍ/ቤት የተመለሰችና በመመሪያው የጨረታ ክፍል የምትሰራ እቢሮዬ አቤቱታ አለኝ ብላ ትገባለች። ኸረ እኔ ተቸገርኩኝ፣ እኚህ አቶ ዳኛቸው የሚባሉ የጠቅላይ ፍ/ቤት አስተዳዳሪ አስቸገሩኝ እኔ ትዳር አለኝ። ምን ይሻለኛል? ብላ ጠየቀችኝ። እኔም በጣም ደነገጥሁ። በቃ ይህ ሰው ፍ/ቤቱን በእግሩ ሥር እያደረገ እየሄደ መሆኑ ቁልጭ ብሎ ታየኝ። ብዙ እንስቶችም ችግር ውስጥ እንደሚገቡ ግልጽ ሆነልኝ። ብቻ ቸገረኝና ለምን ወደ አቶ መንበረ ዘንድ አትሄጅም? ብዬ ጠየኳት። ኸረ እርሳቸው አልተቀበሉኝም አለችኝ። አለቃ ሁልጊዜ ትክክል ነው በሚለው መርህ አቶ መንበረጸሐይ እየታወረ መሄዱንና እንደማይቀበላት እያወቅሁ ነው ግራ ገብቶኝ የማይሆን ጥያቄ ያቀረብሁላት። አቶ ደሣለኝም ሰውዬው ባክህን ትክክል የሚሰራ ነው ይለኝ ጀመር። እስኪ እንግዲህ እከታተላለሁ። ሌላ ምን ማድረግ እችላለሁ አልኳትና ተመለሰች።

አንድ ቀን ለእኔ ደውሎ አቶ ወልደሚካኤል እዚህ ፍርድ አፈጻጸም ሠራተኞችን መከታተል ትታችኋል እንዴ? ብሎ ጠየቀኝ ምነው? አልኩት። ይህች ሰላማዊት የምትባል ሠራተኛ ጨረታዎችን እያሰናከለች ስታስቸግር ለምን ዝም አላችሁ? ስለኝ እኛ እዚሁ እያለን ባለአቤቱታዎች እንዴት እናንተ ዘንድ ሄዱ? ብዬ መልሼ ጠየቅሁ። አንድ ቦታ አሰናከለች የተባለን አንድ የጨረታ መዝገብ ነገረኝና እየው አለኝ። እኔም ሌላ ምንም ሳልናገር እስኪ መዝገቡን አስመጥቼ እንድማይ ተነጋግረን ተለያየን። በአንድ በኩል ሰላማዊትን ወደ ብሮዬ በሌላ በኩል መዝገቡን አስመጥቼ እያየሁ አነጋገርኳት። እኔ በወቅቱ የገጠመኝን ችግር የፈጸምኩት የአፈጻጸሙ ክፍል ሃላፊውን ጠይቄ ተስማምቶበት ነው። በራሴ ያደረግሁት ነገር የለም አለችኝ። የፍርድ አፈጻጸም ተወካይ ሃላፊውን ደውዬ ጠየቅሁት በጉዳዩ ላይ። እርሱም አዎን በወቅቱ ልጅቷ ደውላ ስትጠይቀኝ ጨረታውን ተግባራዊ እንድታደርግ በቴሌፎን ነግሬአታለሁ አለኝ። በኋላ ይህኑን ለአቶ ዳኛቸው ነግሬ በጣም ተበሳጨ። ኸረ ይህ ብቻ አይደለም ሌሎች ፋይሎች አሉ በሚል ዝርዝሮችን ላከ። እኔም ለነገሩ እዉነቱ ነጥሮ እንዲወጣ በፌዴራል የመጀመሪያ የአስተዳደር ሃላፊ በአቶ አያሌው ተፈራ ሰብሳቢነት አንድ ኮሚቴ ተቋቁሞ እንዲመረምረው አደረግሁ። ከአምስቱ መዝገቦች ትዝ የሚለኝ በዚያች በአፈጻጸሙ ተወካይ ትዕዛዝ የተፈጸመው የጨረታ ሽያጭ ሆኖ ተገኘ። እርሱም ቢሆን የአካሄድ ስህተት እንጂ በፍሬ ውስጥ የሚገባ አይደለም። ታዲያ በአስቸኳይ ርምጃ ተወስዶባት ሊገለጽልን ይገባል አለኝ። ጌቷን የተማመነች በግ ላቷን እውጭ ታሳድራለች ይባል

የለ። እኔ እንደ ከተባለ አጥፊው የፍርድ አፈጻጸም ተወካይ ሃላፊ ነው። በርሷ ላይ ምንም ርምጃ ሊወሰድባት አይገባም ብዬ ስልኩን ዘጋሁ።

በማግሥቱ ገና እቢሮዬ ስገባ ጸሐፊዬ አቶ መንበረ ደውሎ ነበር አለችኝ አገናኝኝ አልኳት። ውዲያኑ አገናኘችኝ። ምነው ፍ/ቤቱን ልታፈርሱ ተነሳችሁ እንዴ? በሚል ጥያቄ ጀመረኝ። እንዴት? የኔ ጥያቄ:: አንድ ወሮበላ ልጅ ለምንድነው ዲፈንድ የምታደርገው? አለኝ። ማነው ወሮበላ? እንዴትስ ነው ዲፈንድ ያደረግሁት? ብዬ መልሼ ጠየቅሁ። አይ ወልዴ ወሰን እያለፍክ መምጣትህን አላወከውም መሰለኝ። የአፈጻጸም ጨረታዎች በሙሉ ተሰናክለው ባለጉዳዮች እሮሮ እያሰሙባት ያለቸውን ልጅ መረን እንድትለቀቅ አድርገሃል። የፍ/አፈጻጸሙም መምሪያ እንዲዘጋ እያደረግህ ነው አለኝ። እኔም እጅግ አናደደኝና እንዴ የፍ/ቤቱ አስተዳዳሪዎች አንተ የምትለው እሮሮ አልደረሳቸውም። እሮሮ ለማሰማት ለሚመጡ ሁሉ ቢሮዬ ክፍት ነው። ጉዳዩ ከተጠርጣሪ መዝገቦች ጋር ተጣርቶ ከአንድ ለዚያውም ከአፈጻጸም ብዥታ በስተቀር ነጻ ሰላማዊት ወጥታለች ካልሁ በኋላ፣ ለመሆኑ አቶ ወልደሚካኤል ቅሬታችንን አይሰማም የሚል ክስ ቀርቦ ነበር? የሚል ጥያቄ አቀረብሁለት በመጨረሻ። እርሱ ግን አባባሌንና ጥያቄዬን ከምንም ሳይቆጥር በቃ ለፍ/ቤቱ የምናደርገውን እርዳታ እናቁም ማለት ነው። ይህች በዚህች ላይ ርምጃ ተወስዶ ማየት ነበረብን እስከአሁን ድረስ። አንተ ግን መልሰህ ክርክርህ ለርሷ ሆነ። እናንተ ርምጃ መወሰድ ካልቻላችሁ እኛ እንወስዳለን እንዳለኝ አበቃን። በኔ ላይ ሊመጣ የሚችለው በራሴ ላይ ነው የሚቀረው፤ ግን በሰላማዊት ላይ የሚደርሰው ርምጃ እስከ ከሥራ ማባረር ሊሄድ እንደሚችል ገመትሁ። ጥሩ ተግባቢ አስተዳደር ሃላፊው ከአቶ አያሌው ጋር ተመካከርንና እነ መንበረ ከሚፈልጉት ክልል ሰላማዊት ገለል እንድትል አደረግናት።

ቢቸግረኝ አንድ ባንድ ስብሰባ ቦታ ተገናኘንና አንተ ሰው ለምንድ ነው ፍ/ቤቱን የምትበጠብጠው? አርፈህ አትቀመጥም በማለት አምርሬ ተናገርሁት። ታዲያ ምን ታደርገኛለህ በሚል በምንም አልቆጠረኝም። እኔም ለነገሩ ይቆጥረኛል ብዬ ሳይሆን፣ ቢያንስ በዚህ ባለሁበት ፍርድ ቤት ላይ የጀመረውን ጣልቃ ገብነት ባለበት ለማቆም ነው። ይህ እስከ ወጣሁ ድረስ በተወሰነ ደረጃ በስኬት እንደተጓዘ ትዝ ይለኛል።

ቀደም ብሎ በፍርድ ቤቱ ማሻሻያ ፕሮግራም መሠረት የፍ/ቤቱ አስተዳደር በዳይሬክተር ይመራ ዘንድ አንድ የሕግ ረቂቅ ለውይይት ቀርቦ ማሻሻያዎች ተደርጎበት ለሚመለከተው ክፍል ቀርቦ ውሳኔው ይጠበቅ እንደነበረ ትዝ ይለኛል። ለቦታው ብቁ ከሚያደርጉት ክራይቴሪያዎች አንዱ የሕግ ዕውቀት ነው። አቶ ይኸው ረቂቅ ካልተሻሻለ በስተቀር አቶ ዳኛቸው የሕግ ዕውቀት የለውም። እስከ አገሬንና ፍ/ቤቱን ለቅቄ እስከወጣሁ ድረስ አቶ ዳኛቸው ካሳ ከአስተዳዳሪነቱ አልፎ ዳኞችንም ለማዘዝ በአቶ መንበረፀሐይ አይዞህባይነት የደረሰ ሰው ነው። ይህን ተጠቃሹን ጽሑፍ ከማየቴ በፊት ስለዳኛቸውና ስለፍ/ቤቱ ይህን ያህልም እንፎርሜሽን አልነበረኝም። ታዲያ ዳኛቸው የፍ/ቤቶቹን የዳይሬክትርነት ቦታ ማግኘቱ አልደነቀኝም። የገረመኝ በአጭር ጊዜ መጋለጡ ነው።

እኔ በዚያ አያያዝና አጀማመር አጉል ባህል ሆነና አፍነው ካላስቀሩት በስተቀር ዳኞቸው የደፈራቸው፣ ያስጨነቃቸው የፍ/ቤቱ ሴት ሰራተኞች ይኖራሉ ብዬ እገምታለሁ። ቅሬታቸውን የሚሰማ የለም። ወደ አቶ መንበረ ቢገቡ አባይ አድርጓቸው ያባርራቸውል። ትንሽ ለመቋቋም እየሞከረ የነበረው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አስተዳዳሪ አቶ አያለው ችግር ውስጥ መግባቱን ይነግረኝ ነበር፤ እኔ ነኝ እዚህ ያደረስክሁ እያለው።  የከፍተኛ ፍ/ቤት አስተዳደር ሃላፊዋ ግን በቁጥጥሩ ሥር በመግባቷ ወደ ውጭ ለጉብኝት እስከመላክ ደርሳልች። አጣብቅኝ ውስጥ ያሉ ዳኞች

እያሉ፣ ጌታው አቶ መንበረ እንደዞረው በሥራ ጉብኝት ይህ ሰው በየአለም አገሩ እየዞረ ነው።

ይህ እንዲህ ሲሆን፣ ከፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት እንኳን ለጉብኝት አንድ አገር ያልወጡ ዳኛ ሆሳዕናና ዳኛ ጌታቸው ምህረቱ ይገኛሉ። ዳኛ ሆሳዕና በፍርድ ቤቱ አስተዳደር ጥርስ ገብታ ወደ ወጭ ለጉብኝት እንዳትወጣ የተፈረደባት ከምርጫው ጋር በተያያዘ ጉዳይ በከፍተኛ ፍ/ቤት በተሰጠ ውሳኔይግባኝ ላይ የልዩነት ድምጽ በመስጠቷ እንድሆነ በውቅቱ ተረድቻለሁ። የከፍተኛው ፍ/ቤት ለቅንጅት የፈረደውን በልዩነት በማጽደቋ መሆኑ ነው። ይህንኑ እግረ መንገዴን አነሳሁ እንጂ በተለይ የፍርድ ቤቱን ገጽታ በሚመለከት ወደፊት የማቀርበው አንስተኛ የሆነ ጽሁፍ ይኖረኛል በነገራችን ላይ፣ በኢትዮጵያ በሥራ ጉብኝት ሰበብ ከሞላ ጎደል የዓለም አገሮችን ያካለለው ባለሥልጣን መንበረፀሐይ ነው ብቻ ነው ብዬ ደፍሬ እናገራለሁ። የሚለጥቀው የፌዴራል የመጀመሪያ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንትና የመንበረ ቀኝ እጅ ደሣለኝ በረሄ ነው። ዳኞች በአስተዳደር አካባቢ እርሱ እንደፈለገው የማይታዘዙት ላይ ሁሉ እንደፈለገው ማድረግ ጀመረ።

ዳኛቸው ቀደም ብሎ በመብራት ኃይል ውስጥ የአንድ ቦታ ሃላፊ ሆኖ ሲሰራ በነበረበት ወቅት ሙስና ፈጽሞአል ተብሎ እንደተባረረ በአንድ የግል ጋዜጣ ላይ ወጥቶ እንደነበረ አስታውሳለሁ። እንዲህ ዓይነቱ ዜና ደርሶ፣ በየጊዜውም ከሠራተኞች እሮሮ ቢሰማም የጠቅላይ ፍ/ቤቱ አስተዳደር ከምንም ሳይቆጥረው አልፎት ለትልቅ ሹመት አብቅቶታል። ሰላማዊት በወቅቱ እንደነገረችኝ፣ ከአንድም ሁለት ጊዜ ወደ አቶ መንበረ ፊት ቀርባ አልበገር ስላለችው የማደርግሽን አውቃለሁ እያለ ቁም ስቅሏን እንደሚያሳት ተማጽኖ ብታቀርብም፣ እንዲያውም ሁለተኛ ቢሮው እንዳትገባ መደረጓን ገልጻልኛለች። እሮሮርችና ቅሬታዎች ከሰራተኞች በየጊዜው ለአስተዳደሩ ሃላፊ ለአቶ መንበረጸሐይ ታደሰ ቢደርሰውም፣ ምንም ፋይዳ ሳይኖረው ለእንዲህ ግላጭ ውጤት በቃ።

<u>ግላጭ የወጡ እንዲህ ዓይነቶች ድርጊቶች እየተፈጸሙ እየታየ ለምንድነው አቶ መንበረጸሐይ በዚህ ሰው ላይ ርምጃ እንዲወሰድ ያላደረገው? የሚለው ጥያቄ ወደ አእምሮአችሁ ብቅ እንደሚልባቸው ይገባኛል።</u>

ከፍ ሲል ጠቆም ለማድረግ እንደሞከርሁት፣ አቶ መንበረ በጉብኝት ያልደረሰበት አገር በጣም ጥቂት ነው። የአገሪቱ ልዩና ቁልፍ ሰው መሆኑ ነው።በወጣም ቁጥር ከአገሪቱ የውጭ ምንዛሪ የሰበሰበው ገንዘብ ከመካከለኛ ነጋዴዎች ተርታ ምናልባትም ሳያስተካክለው እንደማይቀር እገምታለሁ። አቶ መንበረ ከመንግሥት በተሰጠ የተንጣለለ ግቢ ባለው ትልቅ ቤት ውስጥ እየኖር ይገኛል። የመኖሪያ ቤት የሌላቸው ግለሰቦች እንዲሰሩ መንግሥት በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች የተወሰነ ካሬ ሜትር ይሰጣል። በዚህ መሠረትም አቶ መንበረ አስቀድሞ ቦታ ተሰጥቶት የራሱ መኖሪያ ቤት ሰርቶአል። እንደገናም ወደ ቦሌ አካባቢ 500 ካሬ ሜትር ተሰጥቶት ትልቅና ልዩ የሆነ ቤት መስራት እንደጀመረ፣ አንዳንድ የፍ/ቤቱ መኪኖች መቀመጫዎቻቸው እየወረዱ የአሸዋና የሲሚንቶ ማጓጓዣ እንደሆኑ ሰምቻለሁ። ይህ የሚፈጸመው በክርስትና ልጁ በአቶ ዳኛቸው አማካይነት ነው። ከዚህም በላይ አቶ ዳኛቸው ለዚህ ቤት መሥሪያ ከዳኞች ማሰልጠኛ ቋት ገንዘብና የተለያዩ ማቴሪያሎችን ልዩ የወጪ ሰንጠረዥ እየከፈተ እያዋለ ነው የሚል ጭምጭምታ ወደ መውጫየ አካባቢ ሰምቼ ነበር። ይህ በወቅቱ በዳኞች ዘንድ በሰፊው የሚነገር ነው። ሁኔታው ለጸረሙስና ኮሚሽን በተለያዩ መንገዶች ቢጠቁሙም የዝሆን ጆሮ ዓይነት ሆኖ እንደቀረ ወሬውን ያቀበሉኝ ነግረውኛል። ጸረ-ሙስና ኮሚሽን ከመለስ ካልታዘዘ በስተቀር፣ በራሱ የሚፈጽመው ምንም ነገር እንደሌለ በከፍተኛ ደረጃ ይነገራል። ተጠቃሹን ምስጢራዊ ድርጊት

ሊያወጡ ይችላሉ ተብለው ወይም ድርጊቱን የተቃወሙ የመበታተንና ሞራላቸው እንዲመታ የመደረግ ዕጣ እንደደረሰባቸው በኮሚሽኑ ሥራ ላይ ሆኜ ሰምቻለሁ። በአጠቃላይም ለፌዴራል ፍ/ቤት ሠራተኞች በአሁኑ ጊዜ ምንም ማንም ጠባቂና አይዞህ ባይ የሌለው መሆኑን ይጠቁማል።

በአጠቃላይም በአሁኑ ጊዜ የፍ/ቤቱ አስተዳደር ሂዶ ሂዶ የወደቀው፣ መሪ ሁልጊዜ ትክክል ነው(The boss is always right) የሚለውን የፈላጭ ቆራጭነት መፈክር ይዞ በገባው ዳኛቸው ካሣ ሥር ይታያል። ያ ጊዜ ደረሰና ጉዶቹ በከፊልም ቢሆን ይፋ እየወጡ ናቸው። ታዲያ አቶ መንበረፀሐይ ከየሰራተኛውና ከየቦታው በዳኛቸው ላይ ጥቆማ ብቻ ሳይሆን፣ እውነቱ አፍጦ እየታየው ይባስ ብሎ ወደ ላቀ ኃላፊነት ቦታ ከፍ እንዲል ያደረገው ከላይ በተዘረዘሩት ምክንያቶች ዳሆን አይቀርም ለማለት እደፍራለሁ። እኔ እንኳ እስከአሁን ድረስ በውጭው በአጠቃላይ ከኮሚሽኑ ሥራ ጋር ተያይዞ በአገራችን የታየውና እየታየ ያለውን የሰብዓዊ መብትን ጥሰት በሚመለከት ላይ ነበር ስጮህ የነበርሁት። በዚህም ጊዜ ሳላገኝ ቆይቻለሁ። አሁን ግን ለማውጣት ከጀመሩት አነስተኛ ጽሑፌ ጋር በቅርብ ቀን በፍ/ቤቱ የሚሠራውንን የማውቃቸውን ለሕዝብ እይታ አበቃለሁ ብዬ እገምታለሁ።

ከፍ ሲል ለመጠቆም እንደሞከርሁት በዚህ ሰው የፆታዊ ትንኮሳ የደረሰባቸውና የሚደርስባቸው ሴት ሠራተኞች አያሌ እንደሚሆኑ እገምታለሁ። ስለዚህ አገር ወዳዶች፣ የሰብዓዊ መብት ተማጓቾች፣ ጠበቆችም ጭምር በጽናት ይህን በፍ/ቤቱ ሴት ሰራተኞችና አጠቃላይ በፍ/ቤቱ ላይ የሚደርገውን ግፍ ለመቅረፍ፣ ብሎም የዲሞክራሲ መሰረት የሆነውን ፍ/ቤት ለማዳን መረባረብ መነሳሳት ይኖርባቸውል።

ኢትዮጵያ ውድና ውብ አገራችን አንድ ናት፣ ሕዝቦችዋም ሁሉ ኩሩና አንድ ናቸው፣ አምላክም ይጠብቃታል፣ ከማጡም ያወጣታል። አንድ እንደሆንን እንዝለቅ፣ አንድነት ኃይል ነውና።

ወልደሚካኤል መሸሻ
2 አፕሪል 2008